# ውጤት የሚያመጣና ሊሰራ የሚችል መዋቅር መመስረት

## አጭር መግለጫ

የሲያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች በአገሪትዋ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጥሩ ትምህርትቤቶች አንዱ ነው፤ ሆኖም ግን የበለጠ እድገትና መሻሻል ለማምጣት በምናደርገው ጥረት በአሁኑ ሰአት ያሉን አሰራር፤ አወቃቀርና የቴክኖለጂ አጠቃቀም መሰናክል ፈጥረውብናል።ስለሆነም የበለጠ ጥራት ያለው አስራርና የበለጠ አገልግሎት ለመሰጥት መዋቅራችንን በበለጠ ማሻሻልና ማጠናከር አለብን።ለሁሉም ተስማሚ የሆነ አሰራር እንዲኖረን ያስፈልጋል፤ለምሳሌ ስለ እያንዳንዱ ተማሪ ችሎታ እድገትን ውጤት ለማወቅ ጥያቄ በምናቀርብበት ጊዜ በተሎ አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጥ የሚችል አስራር እንዲኖረን ያስፈልጋል፤ በዲስትሪክቱ ስራ ለማመልከት ያለው አስራር ለሁለም ቀላል እንዲሆን ማድረግ፤ ገንዘባችን በተገቢው ቦታ ስራ ላይ እንደዋለና እንዳልዋለ ለመቆጣጠር የሚያስችለን ጥሩ አሰርር እንዲኖረን ማድረግ።

ያሉንን ፕሮግራሞችና ወጪዎች መቆጣጠርና በቅርብ ክትትል ማድረግ እንዲሁም ፈጣን የሆነ አስራር እንዲኖረን በማድረግ የሲያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ለሁሉም ተማሪዎችና ትምህርትቤቶች ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጥ የትምህርትቤቶች ክልል እንዲሆን ማድረግ።

## ዋና አስፈላጊ ነገሮች

በዚህ አመት የበለጠ ትኩረት የሚሰጣቸው አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉን

**አዲስ ሰራተኛ የመቅጠር አሰራር ላይ ማሻሻል ማድረግ** – የሲያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች አዲስ ሰራተኛ መቀጠር ላይ ያለው አሰራር ከሌሎች ጎረቤት ክልሎች ለየት ያለ አመቺ ያለሆነ አስራር ነው ያለው።በዚሁ ምክንያት ጥራት ያላቸውና ጎበዞች የሆኑ አስተማሪዎች ወደኛ መጥተው ስራ ከማመልከት ይልቅ ወደ ሌላ ክልል ሄደው ለማመልከት ይመርጣሉ።አመልካቾች ወደኛ መጥተው እንዲያመለክቱ የአቀጣጠር አስራራችንን ማሻሻል አድርገናል(ከአስተማሪዎች፤ ርእሰመምህሮችና ሌሎች ሰራተኞች በተገኘው ሃሳብ መሰረት) አዲሱ አሰራር ስራ ላይ እንዲውል አድርገናል።

**አዲሱ ቴክኖሎጂ ማሳደግና ማሳደስ** – በአሁኑ ሰአት የምንጠቀምባቸው አብዛኞቹ የኮምፒዩተር ስስተም ከ1970 ጀምሮ የነበረና ጊዜ ያለፈበት ያረጀ ሲስተም ነው። ይህንን ለማሻሻል የማይቻል አስቸጋሪ ነው።ስለሆነም በአሰራራችን ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሮውብናል። ስለዚህ ካለው አዲስ እድገት ጋር ለመንዝና አስፈላጊ ለውጦች ለማምጣት ያለን የቴክኖሎጂ ሲስተም ማሳደግና እንዲታደስ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።

**የፕሮግራሙ ውጤታማነት ግምገማ** – የሲያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ጥራት ያላቸው ብዙ የተለያዩ ፕሮግራሞች ያሉት በጣም ትልቅ ድርጅት ነው።ሆኖም ግን በአሁኑ ሰአት የፕሮግራሞቹ ጥራት የምንቆጣጠርበት ጥሩ አሰርራ የለንም።ፕሮግራሞቻችን የምንቆጣጠርበት ጥሩ አሰራር እንዲኖረን እንፈልጋለን። መጪው አመት በአዲሱ ባጀት አስራር መሰረት የፕሮግራሞቻችን ጥራት የምንቆጣጠርበት አስራር ይኖረናል።ይህ አሰራር በተለይ ለተማሪዎች በይበለጥ ሊጠቅም የሚችል ስራዎች ለመስራት ያስችለናል።

## ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በይበልጥ ለማወቅ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ?
- የጎደለ ነገር ካለ?
- ስለ አሰራራችን ያሉት መረጃዎች ሁሉ በምን መንገድ እንዲደርሳችሁ ትፈልጋላችሁ?